**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር**

**የቀድሞ ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን**

**የ2014 በጀት ዓመት ከሐምሌ / 2013 እስከ ታህሳስ 30/2014 ሂሳብ**

**ኦዲት ሪፖርት**

**መጋቢት 2015ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**የቀድሞ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር**

**ከሀምሌ2013 - ታህሳስ 2014 ድረስ ያለ የሂሳብ**

**ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት**

የቀድሞ ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቀድሞ ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቀድሞ ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሚኒስቴሩ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የተጠቃለለ የሂሳብ ማመዛዘኛ

## ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የቀድሞ ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሊረጋገጥ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ኮሚሽኑ በቀን 10/3/2014 በኢንቮይስ ቁጥር 00027281 ሀምሳ ለሚሆኑ ከአስተዳደርና ከክልል ከተማ ለመጡ ስፖርት ኮሚሽነሮች ጋር ምክክር ለማድረግ በዮድ አቢሲንያ ለተደረገ የእራት ግብዣ ብር 90,992.72 የተከፈለ ሲሆን የተሳታፊዎች ዝርዝር ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

   ከላይ ከተራ ቁጥር 1 ከተገለጸው በስተቀር የቀድሞ ስፖርት ኮምሽን የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

1. <u>ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች(Compliance Matters)</u>

   በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32፤ በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) መሰረት ለስራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ስራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ እንጂ በመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚሰበሰብ ወይም የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

   - ብር 645,358.60 እስከ አስር ዓመት የቆየ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

## 2. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤

- ስፖርት ኮሚሽኑ ለኢንሹራንስ የፈጸመው ክፍያ በቀን 9/03/2014 በኢንቮይስ ቁጥር 00027221 **በሂሳብ መደብ** 2241104 (6254) ብር **210,707.04** መያዝ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2631101(6412) የተያዘ መሆኑ፤
- በቀን 26/11/2013 በኢንቮይስ ቁጥር 00025713 በሂሳብ መደብ 2251101 ብር 137,817.50 በስልጠና መያዝ ሲገባው በሂሳብ መደብ 2221101በውሎ አበል የተያዘ መሆኑ በድምሩ ብር 348,524.54 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**